# ሃገርን አሳልፎ የመስጠት ፍላጎት የተንፀባረቀበት አቋም

ክፍል አንድ

ኢ.ብሳ ነመራ

08-22-14

የሠማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ይልቃል ጌትነት ሰሞኑን በኢትዮጵያ ተወካይ ላላቸው ሃያ የአውሮፓ ሕብረት አባል ሃገራት አንድ ነገር ሹክ ማለታቸውን ሰምተናል፤ ሃገራቱ በቅርቡ ኢትዮጵያን በተመለከተ በአዲስ አበባ አዘጋጅተውታል በተባለ መድረክ ላይ። የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር እዚህ መድረክ ላይ ተገኝተው ሃገራቱ በኢትዮጵያ ላይ መውሰድ ስለሚገባቸው እርምጃ ሹክ ብለዋልን ሰምተናል። አቶ ይልቃል የአውሮፓ ሃገራት ዚምቧቤ ላይ እንዳደረጉት በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ እንዲጥሉ ተማፅነዋል። ይህን የሰሙ ብዙዎች የሰውየው አቋም "ሃገርን አሳልፎ ከመስጠት ክህደት አይለይም" ሲሉ አድምጫለሁ። በመሆኑም በዚህ ፅሁፍ ላይ አቶ ይልቃል ለህብረቱ አባል ሃገራት ያወሩትን በኢትዮጵያ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ይልቃል ጌትነት ሃያ የአውሮፓ ሃገራት ስለኢትዮጵያ አዘጋጁት የተባለው መድረክ ላይ ተጋብዘው እንደተገኙ ነው የተናገሩት። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ፓርቲያቸውም ሆኑ እርሳቸው ምንም ድርሻ የሌላቸው፣ ገና የፖለቲካ ዳዴ ላይ ያሉ ሆኖ፣ ለዛውም ለወደፊትም ቆመው መራመድ መቻላቸው አጠራጣሪ ለሆኑ ፓርቲና መሪው፣ ከሌሎች ተለይተው ስለኢትዮጵያ እንዲናገሩ መጋበዛቸው ብዙዎችን አስገርሟል። "ከአውሮፓ ሃገራት ኤምባሲዎች ደጃፍ ስለማይጠፉና ጭቅጭቃቸው ሰልችቷቸው።" የሆናል የጋበዟቸው ያሉም አሉ።

ያም ሆነ ይህ አቶ ይልቃል የአውሮፓ መንግስታት ተወካዮች የተባሉ ሰዎች ዘንድ ቀርበው አሁን አለ ስለሚሉት የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታና ስለገዢው ፓርቲ እንዲሁም ኢትዮጵያ ላይ መወሰድ ሰላለበት እርምጃ አውርተዋል።

አቶ ይልቃል ሥለኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሲያወሩ፣ ከዚህ ቀደም እርሳቸውና መሰል ፅንፈኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች ሲያደርጉት እንደነበረው፣ “ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ አፈናና የሰብአዊ መብት ረገጣ ይፈፅማል።” በማለት ነው የጀመሩት። ለዚህ የተለመደ ውንጀላቸው በዋቤነት የጠቀሱት “ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች ታስረዋል” የሚል ወሬ ነው። የአቶ ይልቃልን አቋም ከዚህ ጀምረን እንመልከተው።

እርግጥ ነው በአሁኑ ግዜ በጣት የሚቆጠሩ የሙሉም ይሁን የግማሽ ግዜ ስራቸውን ፖለቲከኝነት ያደረጉ ወይም ‘ፖለቲከኞች ነን’ የሚሉ ሰዎች እንዲሁም ሥራቸው ጋዜጠኝነት የሆኑ ግለሰቦች ክስ ተመስርቶባቸው በእስር ላይ ሆነው ጉዳያቸውን በመከታተል ላይ ናቸው። ቅጣት ተወስኖባቸው በማረሚያ ቤት የሚገኙ ‘ፖለቲከኞች ነን’ ባዮችም አይጠፉም። እዚህ ላይ መታየት ያለበት ዋናው ነገር መከሰሳቸውና በማረሚያ ቤት መገኘታቸው ሳይሆን፣ “በምን ምክንያት ክስ ተመሰረተባቸው? በምንስ ምቅንያት ቅጣት ተወሰነባቸው?” የሚለው ነው።

ፖለቲከኞቹና ስራቸው ጋዜጠኝነት የሆኑ ግለሰቦቸ ክስ የተመሰረተባቸውና በፍርድ ቤት ቅጣት የተወሰነባቸው በያዙት አቋምና አመለካከት ወይም በገለፁት አቋምና አመለካከት ምክንያት አይደለም። አመለካከታቸውንና አቋማቸውን በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር ተደራጅተው በማራመዳቸው፣ አመለካከታቸውንና አቋማቸውን በመግለፃቸው አልጠጠየቁም። የዜጎች የፈቀዱትን አመለካከት የመያዝ፣ የመግለፅ፣ አመለካከታቸውን በግልና በድርጅት የማራመድ መብትና ነፃነት በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ተከብሯል። እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች የተከበሩት በገዢው ፓርቲ ወይም በጠቅላይ ምኒስትሩና በፕሬዝዳንቱ ችሮታ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ ባጸደቀውና የቃል ኪዳን ሰነዱ በሆነው የኢፌዴሪ ሕገመንግስት ነው የተከበረው።

የኢ.ፌዴሪ ሕገመንግስት በአንቀፅ 29 “ የአመለካከትና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት” በሚል ርዕስ ስር፤

- *ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።*
- *ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነተ ሃሳቡን የመግለፅ ነፃነተ አለው። ይህ ነፃነት በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በፅሁፍ ወይም በህትመት በሥነጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውኝ ማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም አይነት መረጃና ሃሳብ የማሰባሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።*
- *የፕሬስና ሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የስነጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶቸ ያጠቃልላል፤*
  - *ሀ. የቅድሚያ ምርምራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣*
  - *ለ. የህዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን፣*
- *ለዴሞክራሲያዊ ሥርአት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የህግ ጥበቃ ደረግለታል።*
- *በመንግስት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችላቸው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።*
- *እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ የዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች፣ እነዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናሉ።*
- *ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦች ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።*

ይላል።

የመደራጀት መብትን በተመለከተም፣ በአንቀፅ 34 **“የመደራጀት መብት”** በሚል ርዕሥ ሥር፤ *“ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ህግ በመጣስ ወይም ህገመንግስታዊ ሥርአቱን በሀገወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።”* ይላል።

እንግዲህ በህገመንግስቱ የተደነገጉ፣ የፈቀዱትን አመለካከት የመያዝ፣ የመግለፅ፣ የመቀበል፣ የማራመድ፣ የመደራጀት . . . መብቶች ምንም ሳይሸራረፉ ተግባራዊ ተደርገዋል። ተግባራዊ መደረጋቸውን ለማረጳገጥ ልዩ ጥናት ማካሄድ አይሻም። በተለያየ አመለካከት

የተደራጁትን እስከ 80 የሚደረሱ የፖለቲከ ፓርቲዎችና አገር በቀል ሲቪል ማህበራት መመልከት አነዱ በተጨባጭ ያለ አስረጂ ነው። እነዚህ ፓርቲዎች በተለያየ የመገናኛ ብዙሃን አቋምና ፖሊሲያቸውን በይፋ እያስተዋወቁ ይገኛሉ። በህዝብ ውክልና ስልጣን ለመረከብ ምርጫ ላይ ይወዳደራሉ። በአገሪቱ ታትመው የሚሰራጩትን የግል መፅሄቶችና ጋዜጦች እንዲሁም የግል የሬደዮ ሥርጭቶችም እንዲሁ በይፋ የሚታዩ አስረጂዎች ናቸው።

እንግዲህ የሠማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ይልቃል ለአውሮፓ ህብረት አባል ሃገራት “ፖለቲከኞች ታስረዋል” ብለው አውርተዋል። እርሳቸው ግን ከገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦቸ የቃል ኪዳን ሰነድ ከሆነው ሕገመንግስት የተለየና የሚፃረር አቋም ይዘው ይህን አቋም ያለምንም ከልካይ ከመሰሎቻቸው ጋር ተደራጅተው በማራመድ ላይ ይገኛሉ። በዚህ አቋማቸው ምክንያት አልታሰሩም፣ አለተከሰሱም፣ አልተቀጡም።

አቶ ይልቃል በበርካታ አጋጣሚዎች “ሕገመንግስታዊው ሥርአት በኃይል መናድ አለበት፣ ይህን ሥርአቱን በኃይል የመናድ እንቅስቃሴ የእኔ ፓርቲ ይመራዋል።” ብለው በይፋ ሲናገሩ ሰምተናቸዋል። ይህ አነጋገራቸው ከፖለቲካ ሥነምግባር አንፃር ፀያፍ በሕግም የሚያስጠይቅ ሆኖ ሳለ በዝምታ ታልፈዋል። በዝምታ የታለፉት እርሳቸው ሥለሚፈሩ ውይም ‘ተፈለጥኩ፣ ተቆረጥኩ’ ብለው ለአውሮፓ ሃገራት ኤምባሲዎች ያሳብቃሉ ተብሎ ሳይሆን፣ የአመለካከት ነፃነትን እንደባህል ማጎልበት አስፈላጊነቱ ሥለሚታመንበት ዜጎች ሃሳባቸውን ሰገልፁ እንዳይሸማቀቁ ለማበረታታት ሆደ ሰፊ መሆን ስላስፈለገ ነው። የአቶ ይልቃል ፓርቲ በየወቀቱ በሚያወጣው መግለጫ በሕዝብ ውክልና ስልጣን የተረከበውን ገዢውን ፓርቲ “ወንበዴ፣ ወሮበላ . . .” በሚል ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ በማይጠበቅ አኳኋን ሲዘልፉ ቆይታል። ይህም በሆደ ሰፊነት ነበር የታለፈው። ሌሎች መሰል የፖለቲካ ፓርቲዎችና አመራሮቻቸውም እነዲሁ ፀያፍና ሕገወጥ ድርጊት ሲፈፅሙ ነው የቆዩት።

ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ዕውን የሚሆንበት የፕሬስ ነፃነትም ሙሉ በሙሉ ተረጋግጧል። ፕሬስን በተመለከተ እንዳለመታደል ሆኖ፣ ይህ መብት ከተረጋገጠበት ግዜ ጀምሮ ታትመው የሚሰራጩት በርካቶቹ ጋዜጦችና መፅሄቶች ነፃ ፕሬሶች ሳይሆኑ በህዝብ ትግል

ምዕራፋቸው የተዘጋውን ዘውዳዊና ወታደራዊ ሥረአቶች በአመፅ የመመለስ አቋም ይዘው የሚንቀሳቀሱ የተቃውሞ ፖለቲካ አራማጆቸ ናቸው። ፐሬሶቹ ራሳቸውን 'ነፃ ፐሬስ' ሳይሆን 'ተቃዋሚ ፐሬስ' ብለው ነበር የጠሩ እንደነበረም እናስታውሳለን።

እነዚህ "ተቃዋሚ ፐሬሶች" ሃሰተኛ መረጃዎችን በማቀረብ፣ በሃሰተኛ መረጃ ህዝብ መንግስትን በጥርጣሬ እንዲመለከት በማድረግ፣ ህዝብን በህዝብ ላይ በማነሳሳት አገሪቱን የሁከትና የብጥብጥ አውድማ ለማድረግ የሚሰሩ ነበሩ። ይህ ብቻ ሳይሆን የአንባቢዎችን የንባብ ጣዕም ባልሆነ መንገድ በመቀረፅ የአገሪቱን የነፃ ፐሬሰ ባህል ከጅምሩ ያበላሹበት ሁኔታም ይሥተዋላል። ፐሬስ፤ ሰለጠረነት፣ አመፅ፣ ብጥብጥ፣ ሥጋት . . . የሚያወራ ተደርጎ እንዲወሰድ አድርገዋል። ከዚህ ጎን ለጎነ ገለልተኛ ሆነው የሁሉንም ወገን አመለካከት የሚያስተናግዱ የግል ሚዲያዎችን "የመንግስት ናቸው፣ የኢህአዲግ ናቸው . . ." የሚል ወሬ በማስወራት ገለልተኝነታቸው ተአማኒ እንዳይሆን በማደረግ የነፃ ፐሬስን እድገት ተፈታትነዋል። ይህ ሁሉ የተቃዋሚዎቹ ፐሬስ አካሄድ በአብዛኛው በሆደ ሰፊነት ነበር የሚታለፈው።

እርግጥ በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባቸው የተቀጡ አሳታሚዎቸ አልታጡም። ይህ የሆነው ግን በግልፅ በህግ የተከለከሉ፤ ህዝብን በህዝብ ላይ የሚያነሳሱ መልዕክት ያላቸው ዐሁፎችን እነዲሁም በሃሰተኛ መረጃ ህዝብን በመንግስት ላይ የሚያነሳሱ መልዕክቶችን በማስተላለፍ ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸው ነው። የክስ ሂደታቸው በይፋ ችሎት በተደረገ የከሳሽ ተከሳሽ ክርክር ነው የተካሄደው። ከዚህ ውጭ ሥራቸው ጋዜጠኛ የሆኑ ግለሰቦች እንደማንኛውም ሰው በፈፀሙዋቸው ሌሎች ወንጀሎ፤ የሽብርተኝነት ወንጀልን ጨምሮ የተቀጡበት ሁኔታ አለ። ይህ ከፐሬስ ነፃነት ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም። ይህን የሚያደረገው ክሱ በሚሰሩበት ወይም በሚያዘጋጁት ጋዜጣ ላይ ያሰፈሩትን ሃሳብ መነሻ ያደረገ አለመሆኑ ነው። ጋዜጠኛ እንደማንኛውም ሰው ጥፋት ፈፅሞ ሲገኝ ይከሰሳል፣ ይቀጣልም፤ ከህግ በላይ አይደለም።

ከነፃ ፐሬስ ምንነት ተቃራኒ የሆነ የተቃዋሚ አመለካከት አራማጅነት ባህሪ አሁንም በግልፅ ይታያል። በሃሰተኛ መረጃ ሕገመንግስታዊ ሥርአቱን ለመናድ የሚያነሳሱ፣ የሃይማኖት ግጭት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ እንዲሁም ብሄሮችን የሚያንቋሽሹ . . . ፅሁፎችን አትሞ

ማሰራጨት መለያ ባህርያቸው የሆኑ ጋዜጦች አሉ። ከእነዚህ ጋዜጦችና መፅሄቶች አሳታሚዎች መሃከል የተወሰኑት ክስ ተመስርቶባቸዋል። ይህ የሆነው ግን በርካቶችን ካስገረመ የረጅም ግዜ ትዕግስት በኋላ ነው። እነዚህ መፅሄቶችና ጋዜጦች ለአመታት ያወጧቸው የነበሩትን ፅሁፎች ሁሉም ዜጋ ያውቃቸዋል። እነዚህን ፅሁፎቸ አንድ በአንድ እየጠቀሱ መተንተን የሚቻል ቢሆንም ለአንድ የጋዜጣ ፅሁፍ ስለሚሰፋ ይዘታቸውን ለማስታወስ ያህል ከመስከረም እስከታህሳስ 2006 በተለይ ፋክት፣ አዲስ ጉዳይ፣ ሎሚና እንቁ ካሳተሟቸው ፅሁፎቸ መሃከል የተወሰኑትን ርዕሦችና የአንዳንዶቹን ደግሞ የዋና መልዕክታቸውን ቅንጫቢ ብቻ እጠቅሳለሁ። እነዚህም፤

*በአዲሱ 2006 ዓመት የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት ሁሉም አካል ሊነሳ ይገባል፤ አገሪቱ የፖለቲካና የስርዓት ለውጥ ያስፈልጋታል፤ የለውጥ ሃዋርያት ወደ አደባባዩ ይጎርፉ ዘንድ ወቅቱ ግድ ብሏል፤ ከኢህአዴግ በኋላ የሚተካው አማራጭ ተዘጋጅቷል? … ይህንን ቀዳዳ አስቀድሞ መድፈኑን አስቸኳይ ያደረገው፣ ለውጡ የሚመጣበት መንገድ ከህዝባዊ እምቢተኝነት ይሆናል የሚለው ቅድመ-ግምት ነው፤ አሁን ባለው ሁኔታ ትግሉን በህዝቡ መካካል በማካሄድ አመፁ ህዝቡ ባለባቸው ቦታዎች በሙሉ በተቀናጀና በተፋጠነ መንገድ ማካሄድ ያስፈልጋል፤ መንግስት ያለው በጠመንጃ ነው፡፡ ህዝብ የመረጠው መንግስት አይደለም፤ ህዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ አቅም መገንባት ያልቻለ መንግስት፣ የተሻለ የዲፕሎማሲ አቅም የሌለው ገዥ ፓርቲ፣ የፖለቲካ ማሻሻያዎችን ለማድረግ የማያስብ አስተዳደር ተሸክሞ ከመኖር አንዴ ሸክሙን አራግፎ መገላገል ይሻላል - አለበለዚያ እኛ የአባቶቻችን ልጆች አይደለንም ማለት ነው፤ በአገሪቱ ታሪክ በሰላማዊ የትግል መንገድ ወይም በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስርዓት ሲለወጥ አይተን አናውቅም፤ ስለዚህ ይህንንም ስርዓት ለመለወጥ ካለፉት የስርዓት ተሞክሮዎቻችን ልንማር ይገባል፤ የለውጥ መንገዶች ሁሉ ሄደው ሄደው ወደአደባባይ የሚገፉ ሆነዋል፤ መንግስትን ተሸክሞ ከመኖር አንዴ አራግፈን ካልጣልን የአባቶቻችን ልጆች አይደለንም፤ ለለውጥ ካልተነሳን ስደቱ፣ ርሃቡ፣ ችግሩ፣ የተበላሸው ፖለቲካ ይቀጥላል፤ በተበከለ ትዕዛዝ የቆሰለ ህዝብ የሚፈወሰው ንፅህናው በተጠበቀ አዲስ መንግስትና አዲስ ትዕዛዝ በመሆኑ ተቃውሞህን በወቅቱ ማፈንዳት አማራጭ የሌላው ነው፤*

የሚሉ ናቸው።

ከእነዚህ ፅሁፎች መፅሄቶቹ ምን ያህል ህገመንግስታዊውን ሥርአት ለመናድ አመፅ ይቀሰቅሱ እንደነበረ መረዳት ይቻላል። ይህ ሁሉ ሲፃፍ ለረጅም ግዜ በሆደ ሰፊነት ታልፏል። እዚህ ላይ ቅር የሚያሰኝ ነገር ቢኖር አሁን የመፅሄቶቹ አሳታሚዎቸ መከሰስ ሳይሆን፣ ይህን ያህል ግዜ ሕግ ሲተላለፉ በዝምታ መታለፋቸው ነው።

እንግዲህ አቶ ይልቃል 'አፈና ይፈፀማል፣ ጋዜጠኞች ይታሰራሉ' የሚሉት ይህ ከላይ የተጠቀሰው የፕሬሰ አካሄድና የመንግስት ታጋሽነት ባለበት ሁኔታ ነው። አቶ ይልቃል መንግስትን የወቀሱላቸው የአውሮፓ መንግስታትም ቢሆኑ የዚህ አይነት ፕሬሶችን ለአንድ ቀን እንኳን እንደማይታገሱ እነሱም ያውቃሉ፤ እኛም እናውቃለን።

አቶ ይልቃል ኢትዮጵያ ላይ ሁሉን የማደረግ ሥልጣን ያላቸው ለሚመስሏቸው የአውሮፓ አገራት ተወካዮች በደፈናው "አፈና ይፈፀማል" የሚል ክስ ከማቅረብ ይልቅ፣ እስከአሁን በተከሰሱትና ቅጣት በተላለፈባቸው ጋዜጠኞችና ፖለቲካኞች ላይ ለፍርድ ቤት የቀረበውን የጥፋተኝነት ማስረጃ፣ እንዲሁም ተከሳሾቹ ያቀረቡትን የመከላከያ ማስረጃ ጠቀሰው ከተከሰሱበትና ከተቀጡበት ይህግ አንቀፅ ጋር አነፃፅረው ማቀረብ ይገባቸው ነበር። እውነት ፍትህ ተዛብቶ ከሆነ በዚህ መንገድ ነበር ማረጋገጥ የሚችሉት። ይህን አላደረጉም፤ የማድረግ ፍላጎት ያላቸውም አይመስለኝም።

እንግዲህ የአውሮፓ ሃገራት እነደ መላዕክት እንከን የለሽ፣ እንደአምላክ ፈራጅ የሚመስሏቸው የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበረ አቶ ይልቃል፣ የአውሮፓውያኑን ሆድ ለማባባት ከላይ የተገለፀውን "አፈና፣ እስር፣ ምንትስ፣ ቅብጥርስ" የሚል ወሬ ከነዙ በኋላ ወደ ሌላ ማብራሪያ ተሸጋግረዋል።

አቶ ይልቃል "ሥለኢህአዴግ ምን ያስባሉ?" ተብለው ተጠይቀው እንደነበረም ሰምተናል። አቶ ይልቃልም "ኢህአዴግ በራሱ ችግር፣ በርዕዮተ ዓለም መደናበር፣ በአመራር ብቃት ማነስ ውስጥ ነው ያለው።" የሚል ምላሽ መስጠጣታቸውንም እንዲሁ ሰምተናል። እርግጥ ኢህአዴግ አቶ ይልቃል እንዳሉት ይሆን?

እውነታው እንዲህ ነው። ኢህአዴግ የጠራ ርዕዮተ ዓለም አለው። የኮረጀው ሳይሆን፣ የኢትዮጵያን ነባራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በሚገባ አጥንቶና ተንትኖ በኢትዮጵያ ልክ ያዘጋኘው የልማታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተዓለም ባለቤት ነው። ይህ ርዕዮተ ዓለም በፓርቲው ውስጥ ሠርጿል። እያንዳንዱ የኢህአዴገ አመራር የልማታዊ

ዴሞክራሲያዊ መርሆችን መተንተን ይችላል፤ በሚያስገረም ብቃት። እያንዳንዱ የፓርቲ አባል ልማታዊ ዴሞክራሲን ርእዮተ ዓለም ምንነት ጠንቀቆ ያወቃል። ትግራይ፣ ኦሮሚያ ፣ አማራና ኦሮሚያ ክልል ያሉ የኢህአዴግ አባላትና አመራሮች ሥለ ልማታዊ ዴሞክራሲ ሲያወሩ አንዱን ከሌላው ለመለየት ያስቸግራል። አመለካከታቸውና አቋማቸው አንድና አንድ ነው። እናም ኢህአዴገ ውስጥ ምንም አይትት የርዕዮተ ዓለም መደናገር የለም። ኢህአዴግ አሁን ሳይሆን የዛሬ አርባ አመት አገሪቱ ምን ደረጃ ላይ እነደምትደርሰ፣ ምን መሠራት እንዳለበት ግልፅ እይታ አለው። በኢህአዴግ ሰፈር መደናገረ የሚባል ነገር የለም።

አቶ ይልቃል በሚመሩት ሰማያዊ ፓረቲ ውስጥ ግን ትልቅ የርእዮተ ዓለም መምታታትና መደበላለቀ ይታያል። ሰማያዊ ፓርቲ ሊበራል ዴሞክራት ነኝ ባይ ነው። ከዚህ በመነሳት መሬት እንደ ጣቃ እየተቀደደ የሚቸበቸብ የግል ንብረት መሆን አለበት የሚል አቋም እንዳለው በተደጋጋሚ ነግሮናል። እዚህ ላይ ሰማያዊ ፓርቲ በቅድሚያ ይህ “መሬት የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ንብረት መሆን አለበት” የሚለው አቋሙ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት ማብራራት አይችልም። ምዕራባውያን ይደግፉታል ከሚል ሃላፊነት ከጎደለው ስሜት የተያዘ ነው። “አሁን ያለውን የአርሶ አደር የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ያስችላል? አነስተኛ ገቢ ላላቸው ከተሜዎች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ማድረግ ያስችላል? በአገሪቱ አሁን በአርሶ አደሩ ይዞታ ሥር የሌለ ሰፊ ለም መሬት አቅርቦት የለም? ወዘተ” የሚሉትን ጉዳዮች ሰማያዊ ፓርቲ ከቁም ነገር አልቆጠራቸውም። ሌሎቸ ሲሉ ሰማ እንደወረደ ተቀበለው፤ በቃ።

በሌላ በኩል ሰማያዊ ፓርቲ መሬተ የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ንብረት መሆን አለበት እያለን፣ በሌላ በኩል መንግስት ለሰፋፊ እርሻ አልሚ የውጭ ባለሃብቶች መሬት በሊዝ ሲሰጥ “ የመሬት መቀራመት” በሚለ ከተቃወሙተ አንዱ ሆነ።

ኢትዮጵያ ከአፌጣጠሯም የተለያየ ባህል፣ታሪክ፣ ቋነቋ . . . ያላቸወ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አገር ነች። ይህ አንድ ሰው ወይም በሀድን (የፖለቲካ ድርጅት) ያደረገወ አይደለም። ያለና የነበረ ነው። ሰማያዊ ፓርቲ ይህን በተጨባጭ መሬት ላይ እውነት መቀበል ያልፈቀደ ወይም ያልቻለ ፓርቲ ነው። ለሰማያዊ ፓርቲ ኢትዮጵያ ብሄራዊ አብዝሃነት ያለባት ህብረ ብሄራዊ አገር ሳትሆን፣ አንድ ብሄርና እምነት ያለባት አሃዳዊ ሃገር ነች። ሰማያዊ ፓርቲ ለብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት ዕውቅና ተሰጥቶ

ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በመከባበርና በመቻቻል ላይ የተመሰረተ አንድነት መኖራቸው አገሪቱን የሚበታትን ሆኖ ነው የሚታየው።

ሰማያዊ ፓርቲ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በተራራ፣ በገደል፣ በሸለቆ . . . ተሸንሽነው በከፋፍለህ ግዛ ሥልት ማንነታቸው ተደፈቆ በአንድ ብሄራዊ ማንነት መለያ በአሃዳዊ ሥርአት መኖር አለባቸው ባይ ነው።

እነዚህ የሰማያዊ ፓርቲ አቋሞች ፓርቲው የርዕዮተ ዓለም መምታታት ውስጥ መሆኑን እንዲሁም ነባራዊ ሁኔታውን ያላገናዘበ ርዕዮተ ዓለም ተከናንቦ የሚባዝን መሆኑን ያመለክታል። እንግዲያው የርዕዮተ ዓለም መደናገረ ውስጥ ያለው መነው?

**ይቀጥላል**